# የኢፌዲሪ ኤምባሲ-ካምፓላ

# የዜጎች ቻርተር ይዘት

1. **የቻርተሩ ዓላማ**

- የዜጎች መረጃ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ፣
- ለዜጎች ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠት፣
- ተጠያቂነትን በግልጽ ለማመልከት፣
- ዜጎች ምን ዓይነት አገልግሎት በምን ያህል ፍጥነት ለማግኘት እንደሚገባቸው ለማሳወቅ፣
- ዜጎች በኤምባሲው አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የባለቤትነት ስሜት ተሰምቷቸው አስተያየት፣ ጥቆማና ግብዓት የሚሰጥበት ሁኔታ ለማመቻቸት፣

2. **ራዕይ**

- የአገራችንን ብሔራዊ ጥቅም በማስከበርና ልማት በማፋጠን ከዜጎች ጋር የተጠናከረ ግንኙነት ያለው ተቋም መሆን፤

3. **ተልዕኮ**

- አገራችን ኤምባሲው ከተወከለባቸው አገራት ጋር ያላትን ግንኙነት በማጠናከር፣ የኢንቨስትመንትና ቱሪዝም ሀብት በማስተዋወቅ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ከአገራቸው ጋር ጠንካራ ትስስር እንዲፈጥሩ መስራት፤

4. **ዕሴቶች**

- የህዝብ አገልጋይነት - Public Service
- አጋርነት - Partnership Effectiveness
- ተዓማኒነት - integrity
- ሙያዊ ልቀት - Professional

- ቁርጠኝነት - Commitment
- ውጤታማነት - Excellence ናቸው

**<u>የዕሴቶች መግለጫ</u>**

1. **<u>የህዝብ አገልጋይነት (Public Service</u>**)

ዜጎችና ባለድርሻ አካላትን በከፍተኛ ትህትና፣ ቅንነትና ቅልጥፍና ማገልገል ኃላፊነታችንና ግዴታችን ነው፡፡ ይህም በየዕለቱ በምናደርገው ዲፕሎማሲያዊ ተግባራችንን ይገልጻል፡፡ ይህ እሴታችን ደንበኞቻችንና ተጠቃሚዎች በምናስገኘው የእርካታ መጠን፣ እንዲሁም እያንዳንዱን አገልግሎት ለመስጠት ከወሰድነው ጊዜና ጥራት አንፃር የሚለካና በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡

2. **<u>አጋርነት (Partnership)</u>**

እንደ ተቋምና እንደ ግለሰብ የኤምባሲው ተልዕኮና ራዕይ በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ የኤምባሲው ሰራተኞች እርስ በርሳችን እንዲሁም ከሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላትና የልማት አጋሮች ጋር በምንፈጥረው ወዳጅነትና የተቀናጀ አሰራር አጋርነትን እናጎለብታለን፡፡ አጋርነት የዕለት ተዕለት ስራችን መገለጫ ሲሆን ይህም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ራዕይ እና ተልዕኮ በማሳካት ሂደት ባፈራናቸው አጋሮች ብዛት የሚለካ እሴት ነው፡፡

3. **<u>ተዓማኒነት (integrity)</u>**

ለመንግስት ፓሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጥብቅና በመቆም በታማኝነትና በቁርጠኝነት መፈጸም፣ የሀገርንና የዜጎችን ጥቅም በከፍተኛ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት ማስጠበቅ እንዲሁም የአገርንና የኤምባሲውን ምስጢሮች መጠበቅ፣ ከአድልዎ የጸዳ ግልጽ አሰራር መዘርጋት ፍትሃዊነት፣ ቅንነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ አኳኋን የኤምባሲውን ተልዕኮና ኃላፊነት በብቃትና ውጤታማነት መወጣትን ይመለከታል፡፡ ይህም የኤምባሲው የስራ ዕቅዶችና ግቦችን ከመተግበርና ከማሳካት አኳያ የሚለካ ይሆናል፡፡

4. **<u>ሙያዊ ህልቀት (Professional Excellence</u>**)

የዲፕሎማሲ ስራዎቻችንን በከፍተኛ መያዊ ብቃትና ክህሎት ማከናወንና ይህንንም በዕለት ተዕለት በምንፈጽማቸው የስራ ውጤቶች ጥራት እንዲለካ ማድረግ፣ የኤምባሲው ተልዕኮ ለማሳካት በየጊዜው በዕቅዶች አፈፃፀምና ኤምባሲው በሚከታተላቸው አገራት ወቅታዊ ሁኔታ ላይ የመረጃ ልውውጥ መድረኮች በማዘጋጀት የዲፕሎማቶችን አቅም ማሳደግ፣

5. **<u>ቁርጠኝነት (Commitment)</u>**

ፈጣን ልማት ለማረጋገጥ፣ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የአገራችንን ደህንነትና ሰላም ለማረጋገጥ በቁርጠኝነት መነሳሳት ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም ተቋማዊ ኃላፊነታችንን ለመወጣት በየደረጃው ለሚካሄድ የዲፕሎማሲ ስራ ቁርጠኛ አቋም መያዝ ከሁሉም የሚጠበቅ እሴት ነው፡፡

6. **ውጤታማነት (Effectiveness)**

የዲፕሎማሲ ስራችንንና አገልግሎት አሰጣጣችን በቅልትፍና ከመስራት ባሻገር ስራዎቻችንና አገልግሎታችንን ጥቅም የሚሰጡና ውጤት የሚያስመዘግቡ መሆን ይኖርባቸዋል ፡፡

7. **ተገልጋዮች**

- በዩጋንዳ፣ በሩዋንዳ፣ ቡሩንዲና DRC የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን፣
- የዳያስፖራ የልማት ማህበራት፣
- የአገራችን የመንግስት መ/ቤቶችና የግል ድርጅቶች፣
- የውስጥ ሰራተኞች፣

8. **አጠቃላይ መርሆዎች**

- ቀልጣፋ፣ ጥራት ያለው፣ ውጤታማና አስተማማኝ የመረጃ አገልግሎት መስጠት፣
- ቀልጣፋ፣ ጥራት ያለውና ውጤታማ፣ የፓስፖርት፣ የሰነድ ማረጋገጥ፣ የሊሴፓሴ፣ የድጋፍ ደብዳቤ፣ የውክልና አገልግሎት መስጠት፣
- ላስቀመጥናቸው እሴቶች መገዛት፣
- ለዜጎች ጥያቄዎችና አስተያየቶች ፈጣን ምላሽ መስጠት፣
- ከአድኋዊ አሰራርና ከሥነ-ምግባር ጉድለት የፀዳ አሰራርን መከተል፣
- ለሰጠናቸው አገልግሎቶችና ለወሰናቸው ውሳኔዎች ተጠያቂዎች መሆን፣
- መልካም ተሞክሮዎች ማስፋት፣

9. **የተገልጋዮች መብቶች**

- በኤምባሲው የሚሰጡ አገልግሎቶች የመጠየቅና የማግኘት፣
- የተሟላ መረጃ የማግኘት፣
- በፍጥነትና በቅልጥፍና የመስተናገድ፣

- የተሰጣቸውን አገልግሎት በተመለከተ አስተያየት የመስጠት፣
- ባልተገባ አገልግሎት ቅሬታዎቻቸውን በየደረጃው የማሰማትና ለቅሬታዎቻቸው ምላሽ የማግኘት፣

## 10. <u>ከተገልጋዮች የሚጠበቅ ግዴታ</u>

- ትክክለኛና ታማኝነት ያለው መረጃ አሟልቶ ማቅረብ፣
- ታማኝነት፣
- በአገልግሎት አሰጣጣችን ላይ አስተያየት መስጠት፣

## 11. <u>የሚጠበቁ ስኬቶች (Outcomes)</u>

- የተፈጠረ ጠንካራ የዳያስፖራ ትስስር፣
- በቢዝነስ ፍሰት የተገኘ ተጨማሪ የውጭ ሀብት፣
- ለዜጎችና ተቋማት የተጠበቁ መብቶችና ጥቅሞች፣
- አመለካከቱ የተስተካከለ፣ ሙያዊ ብቃት ያለው፣ ተልዕኮውን የሚፈጽምና መብቶቹ የተጠበቁለት የሰው ሀይል ፣
- በተሰጠ አገልግሎት የጨመረ የተገልጋዮች እርካታ፣
- ኤምባሲው የተወከለባቸው አገራት ስለአገራችን ልማት፣ ሰላምና ዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ደጋፊ አመለካከት፣
- የተገነባ የሀገር ገጽታና የተበራከቱ ደጋፊዎች፣

# የኢፌዲሪ ኤምባሲ ካምፓላ የዜጎች ቻርተር

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ክፍል | የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ | | | አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | ጥራት | ወጪ | |
| | **የፖለቲካ፣ ቢዝነስና ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ዘርፍ** | | | | | |
| 1 | A week in the horn ለተደራሾች በኢሜይልና በድረ-ገፅ እንዲደርስ ማድረክ፣ | የፖለቲካ፣ ቢዝነስና ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ጉዳዮች ክፍል | በሳምንት 1 ጊዜ | | | • በኢንተርኔት በመጠቀም፣ |
| 2 | ወደ አገራችን በሜድ ኢንቨስት ሊያደርጉ የሚፈልጉ ባለሀብቶችና ኩባንያዎች የቅድመ ኢንቨስትመንት ጉብኝተ ለማድረግ አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርጉ የሚችሉ ኢንቨስተሮች በአገር ቤት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እንዲገናኙ ማድረግ፣ | የፖለቲካ፣ ቢዝነስና ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ጉዳዮች ክፍል | | | | • የድርጅታቸውን ፕሮፋይልና ኢንቨስት ለማድረግ የፈለጉትን ዘርፍ በመግለፅ ጥያቄ በፅሁፍ ማቅረብ፣ |
| 3 | ወጪ ምርቶቻችንን በሚመለከት ከዘርፉ ተዋናዮች በሚቀርበው መረጃ ላይ በመመስረተ ለወጪ ምርቶቻችን አዳዲስ ገበያ ማፈላለግ፣<br>የአገራችን ወጪ ምርቶች እንዲገዙ የምናግባባቸው አስመጪዎች ጥያቄ መልስ እንዲያገኝ ማድረግ፣ | የፖለቲካ፣ ቢዝነስና ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ጉዳዮች ክፍል | | | | • የድርጅታቸውን ፕሮፋይልና ከኢትዮጵያ ሊሊያስመጡት የሚፈልጉት ምርት ዓይነትና መጠን በመግለፅ ጥያቄ በፅሁፍ ማቅረብ፣ |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ክፍል | የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ | | | አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | ጥራት | ወጪ | |
| 4 | የተለያዩ ቢዝነስ ኤግዚቢሽኖችና የንግድ ትርኢቶች ላይ ለሚደረግ ተሳትፎና ሌሎች የፕሮሞሽን ስራዎች ድጋፍ መስጠት፣ | የፖለቲካ፣ ቢዝነስና ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ጉዳዮች ክፍል | | | የስልክ ግንኙነት ወጪ | • በአገራችን በሚዘጋጁ ኤግዚብሽኖች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች መረጃው እንዲደርሳቸው ማድረግ፣<br>• ኤምባሲው በሚከታተላቸው አገራት የሚዘጋጁ ኤግዚቢሽኖች በአገር ቤት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት መረጃው ማድረስ፣ |
| | **በዳያስፖራና ቆንስላ ጉዳዮች ዘርፍ** | | | | | |
| 1 | ውክልና የመስጠት አገልግሎት | በዳያስፖራና ቆንስላ ጉዳዮች ክፍል | 45 ደቂቃ | | | • የውክልናው መሠረታዊ ይዘት የሚገልፅ ማመልከቻ ማቅረብ፣<br>• የኢትዮጵያ ፓስፖርት ጊዜው ያላለፈበት ዋናውና ኮፒ፣<br>• የመኖርያ ፈቃድ ዋናውና ኮፒ፣<br>• የዩጋንዳ ወይም የሩዋንዳ ወይም የዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ወይም የቡሩንዲ ዜጋ የሆነ/ች የየአገራቱ ጊዜው ያላለፈበት ፓስፖርትና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ዋናውና ኮፒ፣<br>• በስደተኛ መታወቂያ ወይም በጊዜያዊ የጉዞ ሰነድ የሚኖሩ ከሆነ/ች ውክልናው ሰነድን በተመለከተ ብቻ ይሆናል፣<br>• የስደተኛ መታወቂያ ዋናውና ኮፒ፣<br>• የአገልግሎት ክፍያው 38 የአሜሪካን ዶላር፣<br><br>**NB**. ተገልጋዮች የውክልና ሰነዱ በህግ አዋቂዎች አዘጋጅተው ማቅረብ የሚጠበቅባቸው ቢሆንም ኤምባሲው በተወከለባቸው አገራት ይህን የህግ ቅርጽ የሚያሲዝና አማርኛ የሚፅፍ ባለመኖሩ ተገልጋዮች እንዳይቸገሩ ሲባል ጥቅል የሆነ የውክልና ናሙና ሰነድ ተሰጥቷቸው እንደየጉዳያቸው እንዲያስተካክሉ ተደርጎ የጽህፈት ስራው በኤምባሲው ይሰራል። |
| 2 | **ሰነድ የማረጋገጥ አገልግሎት** | | | | | |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ክፍል | የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ | | | አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | ጥራት | ወጪ | |
| 2.1 | ከኢትዮጵያ የሚመነጩ ሰነዶችን ለማረጋገጥ | በዳያስፖራና ቆንስላ ጉዳዮች ክፍል | 10 ደቂቃ | | | • እንዲረጋገጥ የሚቀርበው ሰነድ ኦርጂናል መሆን አለበት፣<br>• በኢፌዲሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በቆንስላ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ተረጋግጦ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ያላለፈበት መሆን ያለበት ሲሆን፣ ሰነዱን ያረጋገጠው ሠራተኛ አሁንም በስራው ላይ ያለ መሆን አለበት፣<br>• የሰነዶች ፎቶ ኮፒ ማረጋገጥ የግድ የሚያስፈልግበት ሁኔታ ሲኖር ፎቶ ኮፒው ዋናውን ሰነድ በሰጠው አካል ህጋዊና ትክክለኛ ቅጅ መሆኑን እናረጋግጣለን... (This is the true copy of the orginal document which is legal and genuine) የሚል ፅሑፍ ተካቶበት መቅረብ አለበት፣<br>• ሰነዱን እንዲረጋገጥለት የሚፈልገው ተገልጋይ ሰነዱ ማንነቱን የሚገልፅ ሰነድ (ፓስፖርት) በመያዝ በአካል መቅረብ አለበት፣<br>• የሚረጋገጠው ሰነድ የድርጅት ከሆነ ድርጅቱ በህጋዊነት የተመዘገበበት መረጃ (የስራ ፈቃድ ጊዜው ያላለፈበት) እና የድርጅቱ ሃላፊ/ምክትል ሃላፊ ፓስፖርት ዋናውና ኮፒ፣<br>• ሰነዱ የሚረጋገጠው በተወካይ ከሆነ የውክልና ሰነድና የተወካይ ማንነቱን የሚገልፅ ሰነድ በመያዝ በአካል መቅረብ አለበት፣<br>• የሚረጋገጠው ሰነድ በኢፌዲሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በቆንስላ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የተረጋገጠ መሆን አለበት፣<br>• ማንኛውም የሚረጋገጥ ሰነድ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቆንስላ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ኦርጂናል ማህተም ያረፈበት መሆን አለበት፣<br>• ለእያንዳንዱ የሰነድ የማረጋገጫ የአገልግሎት ክፍያ ለኢትዮጵያውያን ለትምህተርት ሰነዶች (Academic Documents) 35 የአሜሪካን ዶላር፣ ለውጭ አገር ዜጎች 65 የአሜሪካን ዶላር፣<br>• ለእያንዳንዱ የሰነድ የማረጋገጫ የአገልግሎት ክፍያ ለኢትዮጵያውያን ከትምህተርት ሰነድ ውጪ ለሆኑ ሰነዶች (Non-Academic Documents) 38 የአሜሪካን ዶላር፣ ለውጭ አገር ዜጎች 68 የአሜሪካን ዶላር፣ |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ክፍል | የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ | | | አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | ጥራት | ወጪ | |
| 2.2 | ከዩጋንዳ፣ ሩዋንዳ፣ ቡሩንዲና ኮንጎ የሚመነጩ ሰነዶችን ለማረጋገጥ | በዳያስፖራና ቆንስላ ጉዳዮች ክፍል | 10 ደቂቃ | | | • እንዲረጋገጥ የሚቀርበው ሰነድ ዋናው ኦርጂናል መሆን አለበት፣<br>• እንዲረጋገጥ የሚቀርበው ሰነድ ከአገሪቱ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ መሆን አለበት፣<br>• የሰነዶች ፎቶ ኮፒ ማረጋገጥ የግድ የሚያስፈልግበት ሁኔታ ሲኖር ፎቶ ኮፒው ዋናውን ሰነድ በሰጠው አካል ህጋዊና ትክክለኛ ቅጅ መሆኑን እናረጋግጣለን… (This is the true copy of the original document which is legal and genuine) የሚል ፅሑፍ ተካቶበት መቅረብ አለበት፣<br>• ሰነዱን እንዲረጋገጥለት የሚፈልገው ተገልጋይ ሰነዱ ማንነቱን የሚገልፅ ሰነድ (ፓስፖርት) በመያዝ በአካል መቅረብ አለበት፣<br>• የሚረጋገጠው ሰነድ የድርጅት ከሆነ ድርጅቱ በህጋዊነት የተመዘገበበት መረጃ (የስራ ፈቃድ ጊዜው ያላለፈበት) እና የድርጅቱ ሃላፊ/ምክትል ሃላፊ ፓስፖርት ዋናውና ኮፒ፣<br>• ሰነዱ የሚረጋገጠው በተወካይ ከሆነ የውክልና ሰነድና የተወካይ ማንነቱን የሚገልፅ ሰነድ በመያዝ በአካል መቅረብ አለበት፣<br>• ማንኛውም የሚረጋገጥ ሰነድ የአገሪቱ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ኦርጂናል ማህተም ያረፈበት መሆን አለበት፣<br>• ለእያንዳንዱ የሰነድ የማረጋገጫ የአገልግሎት ክፍያ ለኢትዮጵያውያን ለትምህትርት ሰነዶች (Academic Documents) 35 የአሜሪካን ዶላር፣ ለውጭ አገር ዜጎች 65 የአሜሪካን ዶላር፣<br>• ለእያንዳንዱ የሰነድ የማረጋገጫ የአገልግሎት ክፍያ ለኢትዮጵያውያን ከትምህትርት ሰነድ ውጪ ለሆኑ ሰነዶች (Non-Academic Documents) 38 የአሜሪካን ዶላር፣ ለውጭ አገር ዜጎች 68 የአሜሪካን ዶላር፣ |
| 3 | በሕይወት የሚኖሩ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ | በዳያስፖራና ቆንስላ ጉዳዮች ክፍል | 30 ደቂቃ | | | • አገልግሎቱን የሚፈልገው ተገልጋይ ጥያቄውን የፅሑፍ ማመልከቻ በመያዝ በአካል ማቅረብ አለበት፣<br>• አገልግሎቱ ያላለፈበት ፓስፖርት ዋናውና ያለበት ኮፒ፣ |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ክፍል | የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ | | | አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | ጥራት | ወጪ | |
| | | | | | | • የመኖርያ ፈቃድ ዋናውና ኮፒ፣<br>• አገልግሎቱን በግንባር ቀርቦና ፎርሞ መቀበል፣<br>• የአገልግሎት ክፍያው 38 የአሜሪካን ዶላር፣ |
| 4 | በዩጋንዳ፣ ሩዋንዳ፣ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክና ቡሩንዲ ሲኖር ሕይወቱ ያለፈ ዜጋን አስከሬን ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ የድጋፍ ደብዳቤ | በዳያስፖራና ቆንስላ ጉዳዮች ክፍል | 20 ደቂቃ | | | • የሟች ፓስፖርት ወይም የስደተኛ መታወቅያ ኮፒ፣<br>• ህይወቱን ያለፈበትን ምክንያት የየሚያረጋግጥ Death Certeficate፣<br>• በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቆንስላ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል አስከሬኑ ወደ አገር ቤት እንዲገባ የሚገልፅ ደብዳቤ፣<br>• አስከሬኑን ወደ አገር ቤት ይዞ የሚሄድ ዘመድ ፓስፖርት ኮፒ፣ ማመልከቻና ሙሉ አድራሻ፣ |
| 5 | በዩጋንዳ፣ ሩዋንዳ፣ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክና ቡሩንዲ ሲኖር ሕይወቱ ያለፈ ዜጋን አስከሬን ህይወቱ ባለፈበት አገር እንዲቀበር የድጋፍ፣ | በዳያስፖራና ቆንስላ ጉዳዮች ክፍል | 20 ደቂቃ | | | • የሟች ፓስፖርት ወይም የስደተኛ መታወቅያ ኮፒ፣<br>• ህይወቱን ያለፈበትን ምክንያት የየሚያረጋግጥ Death Certeficate፣<br>• በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የቆንስላ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል አስከሬኑ ባለበት አገር እንዲቀበር የሚገልፅ ደብዳቤ፣<br>• የሟች አስከሬን ህይወቱ ባለፈበት አገር እንዲቀበር ከቤተሰብ የሚቀርብ ማመልከቻ፣ የጥያቄው አቅራቢ (ቤተሰብ) ፓስፖርት ኮፒ፣ |
| 6 | አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ ውጭ አገር ቆይተው ጠቅልለው ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ታክስና ቀረጥ ከፍለው እቃዎች ለማስገባት | በዳያስፖራና ቆንስላ ጉዳዮች ክፍል | 45 ደቂቃ | | | • በዩጋንዳ ወይም በሩዋንዳ ወይም በዲሞክራቲክ ኮንጎ ወይም በቡሩንዲ አምስት አመትና ከዚያ በላይ መኖራቸውን የሚገልፅ መረጃ ከማመልከቻ ጋር አያይዞ ማቅረብ፣<br>• ወደ አገር ቤት ጠቅልሎ የሚመለስ መሆኑን የሚያሳይ (የመኖሪያ ፈቃድ መመለሱን/ከሚሰሩበት ተቋም) ከሚኖሩበት አገር ጨርሰው መውጣቶን መረጃ ማቅረብ፣<br>• የፓስፖርት ዋናውና ኮፒ<br>• የመኖርያ ፈቃድ ሁለት ኮፒ<br>• የሌላ አገር ዜግነት የያዙ ከሆነ ዜግነት ከተሰጠው አገር የተሰጠ ፓስፖርትና በትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቅያ ካርድ ዋናውና አንድ ኮፒ፣ |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ክፍል | የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ | | | አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | ጥራት | ወጪ | |
| | | | | | | • ወደ አገር ቤት ማስገባት የሚችሉት ዕቃዎች በትክክል ከለዩ በኃላ ይዘዋቸው ለመሄድ የተፈቀደሎትን የእቃ ዝርዝሮ ማቅረብ፣ |
| 7 | በዩጋንዳ፣ በሩዋንዳ፣ በቡሩንዲና ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በአገራችን ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታ ተጠቅመው ኢንቨስት እንዲያደርጉ ድጋፍ ማድረግ፣ የድጋፍ ደብዳቤ መስጠት፣ | በዳያስፖራና ቆንስላ ጉዳዮች ክፍል | 45 ደቂቃ | | | • የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል፣<br>• ጊዜው ያላለፈበት ፓስፖርት ዋናውና ኮፒ፣<br>• የሌላ አገር ዜግነት የያዙ ትውልደ ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያ ተወላጅነት ካርድ ዋናውና ኮፒ፣<br>• ጊዜው ያላለፈበት የመኖሪያ ፈቃድ ዋናውና ኮፒ፣ |
| 8 | የታላቁ ህዳሴ ግድብ ቦንድ ሽያጭ የአገልግሎት መስጠት፣ | በዳያስፖራና ቆንስላ ጉዳዮች ክፍል እና በፋይናንስ ክፍል | 20 ደቂቃ | | | • ቦንዱ የሚሸጠው ለኢትዮጵያውያን ወይም ትውልድ ኢትዮጵያውያን፣ ለአባይ ተፋሰስ አገሮች፣ ለጎረቤት አገሮች፣ ለኢትዮጵያ ወዳጆችና በኢትዮጵያ ውስጥ ኢቨስት ላደረጉ ኢንቨስተሮች ነው፣<br>• ለትውልድ ኢትዮጵያውያን የውጭ አገር ዜጎጭ የትውልድ ኢትዮጵያ መታወቂያ ካርድ፣<br>• በስደተኝነት ተመዝግበው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የስደተኛ መታወቂያ ካርድ፣ |
| 9 | የዳያስፖራና የቆንስላ ጉዳዮች መረጃና የመከር አገልግሎት | በዳያስፖራና ቆንስላ ጉዳዮች ክፍል | 1-10 ደቂቃ | | | • የዜጋ ወይም የደንበኛ ፍላጎት፣<br>• በማንኛውም ዘዴ(በአካል፣ በስልክ ወዘተ …) የምክር/የመረጃ አገልግለት ጥያቄ ማቅረብ፣ |
| | **የኢሚግሬሽን ጉዳዮች ዘርፍ** | | | | | |
| 1 | አዲስ ፓስፖርት ለመስጠት | በኢሚግሬሽን ጉዳዮች ክፍል | 45 ደቂቃ | | | • ዜግነቱ/ቷ በዋናው መምሪያ ተጣርቶ በዋናው መምሪያ በኩል ሲፈቀድ፣<br>• የፓስፖርት መጠየቂያ ቅፅ በመሙላት ማቅረብ፣<br>• ከዚህ በፊት አሻራ ካልሰጡ በኤምባሲው ቆንስላ ክፍል በመገኘት አሻራ መስጠት፣ |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ክፍል | የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ | | | አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | ጥራት | ወጪ | |
| | | | | | | • አራት ፓስፖርት ሳይዝ ፎቶግራፍ ማቅረብ፣<br>• ከኢትዮጵያ ሲወጡ የነበረው የኢትዮጵያ ፓስፖርት ሁለት ኮፒ ማቅረብ፣<br>• ከሚኖሩበት  አገር የተሰጠ መኖሪያ ፈቃድ ዋናውና ሁለት ኮፒ ማቅረብ፣<br>• የስም ወይም የዕድሜ ለውጥ ካለ በፍ/ቤት የተወሰነና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ ማስረጃ ዋናውና ሁለት ኮፒ፣<br>• በአካል መገኘት ያስፈልጋል፣<br>• የአገልግሎት ክፍያ ለባለ 32 ገፅ ፖስፖርት 60 የአሜሪካ ዶላር፣ ለባለ 64 ገፅ ፖስፖርት 110 የአሜሪካ ዶላር፣ |
| 2 | ፓስፖርት ለማሳደስ / ለማስቀየር | በኢሚግሬሽን ጉዳዮች ክፍል | 45 ደቂቃ | | | • የፓስፖርት መጠየቂያ ቅፅ በመሙላት ማቅረብ፣<br>• አገልግሎቱ ያበቃ ፓስፖርት ዋናውና ኮፒ ማቅረብ፣<br>• የመኖሪያ ፈቃድ ዋናውና ኮፒ፣<br>• አራት ፓስፖርት ፎቶግራፍ ማቅረብ፣<br>• አገልግሎቱ ያበቃው ፓስፖርት ሲወስዱ 14 ዓመት ካልሞላቸውና አሻራ ካልሰጡ/በማኑዋሉ ፓስፖርት የቆዩም ከሆነ በአካል መምጣት አሻራ መስጠት ያፈልጋል፣<br>• የአገልግሎት ክፍያ ለባለ 32 ገፅ ፖስፖርት 60 የአሜሪካ ዶላር፣ ለባለ 64 ገፅ ፖስፖርት 110 የአሜሪካ ዶላር፣ |
| 3 | በጠፋ ፓስፖርት ምትክ አዲስ ፓስፖርት ለማግኘት | በኢሚግሬሽን ጉዳዮች ክፍል | 45 ደቂቃ | | | • የፓስፖርት መጠየቂያ ቅፅ በመሙላት ማቅረብ፣<br>• ስለመጥፋቱ የፖሊስ ማስረጃ፣<br>• የጠፋው ፓስፖርት ኮፒ ማቅረብ፣<br>• አራት ፓስፖርት ሳይዝ ፎቶግራፍ ማቅረብ፣<br>• የአገልግሎት ክፍያ ለባለ 32 ገፅ ፖስፖርት 90 የአሜሪካ ዶላር፣ ለባለ 64 ገፅ ፖስፖርት 165 የአሜሪካ ዶላር፣ |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ክፍል | የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ | | | አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | ጥራት | ወጪ | |
| 4 | አዲስ ፓስፖርት ለህጻን | በኢሚግሬሽን ጉዳዮች ክፍል | 45 ደቂቃ | | | • የፓስፖርት መጠየቂያ ቅፅ በመሙላት ማቅረብ፣<br>• ህፃኑ / ህፃኗ ፓስፖርት እንዲሰጠው  እንዲሰጣት የአባትና የእናት ስምምነት ያለበት ማመልከቻ ማቅረብ፣<br>• በአገራቱ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የህፃኑ /የህፃኗ የልደት ምስክር ወረቀት ዋናውና ኮፒ ማቅረብ፣<br>• የህፃኑ /የህፃኗ አራት ፓስፖርት ፎቶግራፍ ማቅረብ፣<br>• የወላጆች ፓስፖርትና መኖሪድ ፈቃድ ዋናውና ኮፒ፣<br>• የአገልግሎት ክፍያ ለባለ 32 ገፅ ፖስፖርት 60 የአሜሪካ ዶላር፣ ለባለ 64 ገፅ ፖስፖርት 110 የአሜሪካ ዶላር፣ |
| 5 | የይለፍ ወረቀት ሊሴ ፓሴ | በኢሚግሬሽን ጉዳዮች ክፍል | 1 ሰዓት | | | • ማመልከቻ ማቅረብ፣<br>• በትክክል የተሞላ የይለፍ ወረቀት መጠየቅያ ቅፅ መሙላት፣<br>• አራት ፓስፖር ሳይዝ ፎቶግራፎች፣<br>• ኢትዮጵያዊ ስለመሆኑ/ኗ የሚያረጋግጥ ፓስፖርት፣<br>• ፓስፖርት ከሌለ ከዋናው መምሪያ ዜግነቱ/ቷ ሲረጋገጥ፣<br>• ፓስፖርት የነበራቸው ከሆነና ፓስፖርቱ ከጠፋባቸው ከዋናው መምሪያ መውሰዳቸውን ሲረጋገጥ፣<br>• በአካል መገኘት ያስፈልጋል፣<br>• የአገልግሎት ክፍያ 50 የአሜሪካ ዶላር፣ |
| 6 | አዲስ የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ለማግኘት | በኢሚግሬሽን ጉዳዮች ክፍል | 1 ሰዓት | | | • መታወቂያውን ለማግኘት ዜግነት ከወሰደበት አገር የተሰጠው አገልግሎቱ የፀና ፓስፖርት ማቅረብ፣ |

| ተ.ቁ | የሚሰጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱ የሚሰጥበት ክፍል | የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ | | | አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠየቅ ቅድመ ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጊዜ | ጥራት | ወጪ | |
| | | | | | | • የአመልካቹ አግባብ ካለው አካል የተረጋገጠ የልደት ምስክር ወረቀት ማስረጃ ኦርጅናል ማቅረብ፣ወይም<br>• የአመልካቹ የቀድሞ የኢትዮጵያ ፓስፖርት ቅጂ፣ ወይም<br>• የወላጅ (አባት/እናት) ፓስፖርት ወይም የኢትዮጵ ነዋሪነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፣ ወይም<br>• አግባብነት ካለው አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የወላጆቻቸው የወራሽነት ማስረጃ ቅጂ፣ ወይም<br>• ስልጣን ካለው ፍ/ቤት የተሰጠና አግባብ ባለው አካል ተረጋግጦ የቀረበ የጉዲፈቻ ማስረጃ ቅጂ፣<br>• ሁለት በቅርብ ጊዜ የተነሳ ሙሉ ፊት የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፣<br>• ለዚህ ዓላማ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ማቅረብ፣<br>• የአገልግሎት ክፍያ 200 የአሜሪካ ዶላር፣ |
| 7 | አካለ መጠን ላልደረሱ የኢትዮጵያ ተወላጅ ልጆች ስለሚሰጥ አገልግሎት | በኢሚግሬሽን ጉዳዮች ክፍል | 1 ሰዓት | | | • የልጁ/ጇን ህጋዊ የልደት የምስክር ወረቀት፣<br>• አገልግሎቱ የፀና ፓስፖርት፣<br>• የወላጁ/ጇ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ፣<br>• የልጁ/ቷ በቅርብ ጊዜ የተነሳው/ችው ሙሉ ፊት የሚያሳይ ፎቶ፣ |
| 8 | የኢትዮጵያ ተወላጅ መታወቂያ ካርድ እድሳት | በኢሚግሬሽን ጉዳዮች ክፍል | 1 ሰዓት | | | • ዜግነት ያገኙበት ሀገር የፀና የዜግነት ፓስፖርት ኮፒ፣<br>• ቀደም ሲል የተሰጠው የኢተዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ኮፒ፣<br>• የአገልግሎት ክፍያ 200 የአሜሪካ ዶላር፣ |